# የትራንስፎርሜሽኑ መዘዝ

ይሄይስ አእምሮ

በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያን ከድህነት ለዘመናት ጨንፍሮ ከያዛት ድህነት ለማላቀቅ የኢሕአዴግ መንግሥት የትራንስፎርማሽን ዕዋጅ በቅርቡ ማወጁ የሚታወቅ ነው:: ጥሩ መመኘት ጥሩ ነው:: ዕዋጁ እንደስካሁኖቹ የግብር ይውጣና የማሞኛ ዕዋጆች ሆኖ የማይቀር ከሆነ ሀገርና ሕዝብ ለሸዎች ዓመታት ተዘፍቀውበት ከነበሩበት የድህነት አዘቅትና የችግር አዙሪት መዉጣታቸው ከሰይጣን በስተቀር የማያስደስተው ስለሌለ ሁላችንንም እሰዬው የሚያስኝ ዕፁብ ድንቅ ነገር ነው:: ይሁንና ካለፈ ልምዳችን ተነስተን ይህን አዲሱን የወያኔ መንግሥት ተምኔታዊ የሚመስል ዕዋጅም ሆነ ከዚያ በፊት በሌሎች መንግሥታት ሳይቀር ታዉጀዉ የነበሩ የበርካታ ዕዋጆችን የመጀመሪያም ሆነ የመጨረሻ ዕጣ ፋንታ ስናይ ተግባራዊነታቸውና ሕዝባዊ አመኔታቸው ብዙውን ጊዜ ጥያቄ ዉስጥ እንደገባ ነው:: የአሁኑም ዕዋጅ፣ መንግሥት ላለፉት 19 ዓመታት ተሞኝተው ያልተሞኙለትን የኢትዮጵያን ሕዝብና «ዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ» ለማዘናጋት የታለመ እስካልሆነ ድረስ ምኞታዊ ጅማሬው መልካም ነው::

ወደ መራሩ ሀገራዊ እውነት እንምጣና አንዳንድ አሣዛኝና አስቂኝ ድራማዎችን እንመልከት:: በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ችግርንና ችጋርን ከሀገር ጠራረጎ ለማስወጣት ቃል በተገባበት በዚያ የአዲስ ዓመት መቀበያ ሌሊት በሚሌኒየም አዳራሽ በተደረገው የነማሞ ቂሎ ድህነትን የመሰናበቻ ዝግጅት ላይ የነሠራዊት ፍቅሬን ቧልታይና ድንቃይ ጭውውት የተመለከተ ጤናማ ዜጋ በርግጥም የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንኛ መቀለጃ እንደሆነ መገንዘብ አይሳነውም:: ምንም ዓይነት ተጨባጭ የሆነ ተስፋ ሰጪ ነገር በሌለበት የድህነት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ተቀምጦ ትራንስፎሮሜሽን በሚሉት የማጭበርበሪያ ፌዝ ሕዝብን ለማደናገር መሞከር ትርፉ ለጊዜው ትዝብት ቢሆንም እየዋለ እያደረ ሲኬድ ደግሞ ቅሌትን ያስከትላል - ቅሌትና ውርደት ለሚገባው ወገን:: ሥሪቱ ውሸትና ትዕቢት የሆነው የወያኔ መንግሥት ግን ማፈር ብሎ ነገር ዕርሙ ነውና በወቅቱ የሚደቀንበትን አንዳች ችግር እሱው ራሱ በውሸልሸል በሚፈጥረው ዘዴ ለማለፍ ይውተፈተፋል እንጂ ስለ ነገው በፍጹ-ም አይጨነቅም፤ በመሆኑም የዕቅዶች እውናዊነት ቅንጣት አያሳስበውም፤ በዚያ ላይ የኢትዮጵያዊነት አጀንዳ ምኑም ስላልሆነ በሀገርና በሕዝብ ጉስቁልና ይደሰት እንደሆነ እንጂ «ሀገር ተራቆተ፤ ሕዝብ ተራበ» ብሎ በምንም መንገድ አያዝንም - ተፈጥሮውም አይፈቅድለትም:: ሀገር ለማጥፋት የመጣ የወሮበላ ግሪሳ ለሰው እንዲያዝን መጠበቅም የዋህነት ነው::

ትራንስፎርሜሽንን መተግበር እንኳንስ ኢትዮጵያዊ መንግሥት በሌለባት በኢትዮጵያ የተረገመ ምድር ይቅርና ለሚመሩት ሀገርና ሕዝብ ሌት ከቀን የሚጨነቁ ውዱዳንና ፍቁራን መሪዎች ባሉባቸው በአንጻራዊነት ሁኔታ ያደጉ ናቸው በሚባሉ ሀገሮች እንኳዋን በጣም አስቸጋሪና ከባድም እንደሆነ ብዙዎች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው:: ደግነቱ የወያኔ ዓላማ ግልጽ መሆኑ በሁሉም ዘንድ ይታወቃል እንጂ እንደ ኢትዮጵያና ሶማሊያ ወይም ጂቡቲና ሄይቲ ያሉ ድኩማን መሪዎች ያሉባቸው ሀገሮች ከመሬት ተነስተው - ድንገት ባንነው - የ«ትራንስፎርሜሽን» ዕዋጅ ነጋሪት ሊያሰጎስሙ አይቻላቸውም - «ለማያውቃችሁ ታጠኑ» ነዋ የሚባሉት! «ስንትና ስንት ክፍለ ዘመን ተኀልተው - (*ተኝተው ማለትም ይቻላል*) - አሁን ምን አገኙና በድንገት የሱሪ ባንገት ዕዋጅ ማስነገር ቻሉ?» ብለን ብንጠይቃቸውም መልስ አይኖራቸውም:: ከፈለገ «ሰማይንና ምድርን ማገናኘት እችላለሁ» ሊል የሚችለው የወያኔው የማፊያ መንግሥት በአምስት ዓመት ውስጥ ያን ሁሉ ቅዠት አከናውናለሁ የማለቱን ቀልድ በወዘ የለሽ ቀልድነቱ እንያዘውና በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ጥቂት የልማት ፍንጭ ለማሳዬት ለተለመው ትልም የሚያግዝ ገንዘብ ለማግኘት ከአቀደባቸው ሥልቶች አንዱን እንመልከት::

የሀገሪቱ ገንዘብ የሆዳም ባለሥልጣናቱን ኪስ ሞልቶ፣ የተቀለለባትን ዕዳዎችና የመንግሥት ሠራተኞችን ደመወዝ ከፍሎ፣ የማፊያው ቁንጮ ለአሠርት ዓመታት በብረትና በባሩድ ታጥሮ ያፈተተውን የሚሠራበትን ወንበር ለማስጠበቅ ለነጭ ለባሾችና ለ'ሎቢስቶች '

እንዲሁም ለሕዝብ ቀጥቃጭ የፌደራል ፖሊስ መሃያ ከፍሎ፣ ባጀትን በቅጡ ሥራ ላይ ለማያውሉ ክልሎች «ባለሥልጣናት» ያለ ሕጋዊ ደረሰኝ ለሚወራረድ የውሎ አበልና በዬቀኑ በነዚሁ ባለሥልጣናት ለሚቃም ጫትና ተጓዳኝ ወጪዎችን ከፍሎ፣ አጠቃላይ የገማ ሥርዓቱን ለማቆዬት በአንድ ጎሳ ወይም ብሔረሰብ የዕዝ ሰንሰለት ብቻ የተዋቀረውን ጎጠኛ ሠራዊት ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ከፍሎ ፣ የቀረውን እናንተው ጨምሩበት . . . የሚተርፈው በጣም ኢምንት ነው፤ በዕርዳታና በብድር ይገኛል ተብሎ የሚጠበቀው ገንዘብም በብዙ ቅድመ ሁኔዎች መሃል የተሻጠ በመሆኑ አያስተማምንም፡፡ ስለዚህ ሕገ ወጡ የማፊያ መንግሥት ያለው አማራጭ በጫካ እንደለመደው በመንግሥትነትም እንዳጠናከረው የዘረፋ ውንብድናውን ማጧጧፍ ነው፡፡ ለምንም ዓይነት ዓለማቀፍና ብሔራዊ ሕግ የማይገዛው ወያኔ ከተራ የቁጭ በሉ ማጭበርበርና ዝርፊያ እስከ ማጅራት መምታት ቢሰማራ የሚያግደው ሃይማኖታዊም ሆነ ሞራላዊ አጥር እንደሌለው ጠንቅቀን እናውቃለን - ይህንን ጀብዱ ሥራውንም በዘመናት ዕኩይ ተግባሩ ያረጋገጠው የአደባባይ ምሥጢር መሆኑን በግፍ የተገደሉ ዜጎች የሙታን መንፈሶች ብቻ ሳይሆኑ የሞት ተራችንን እዬጠበቅን የምንገኘው ግፉኣን ቋሚዎችም እንመሠክራለን፡፡ በድብቅም ይሁን በግልጽ ከሚንቀሳቀሱ ሌሎች መሰል የሥራ ባልደረቦቹ ወያኔ የሚለየው በሀገርና በሕዝብ ላይ የሚፈጽማቸውን ማናቸውንም ወንጀሎች በጉልበት የያዘውን መንግሥታዊ ሥልጣን በመጠቀም የሕጋዊነት ጭምብል ማልበሱ ነው - ከሕግ አግባብ ውጪ የተገኘን ገንዘብ በ“money laundering” ሥልት ወደ ሕጋዊ ገንዘብነት ከሚለውጡ ተራ ዓለማቀፍ ወንበዴዎች የወረደ አሳፋሪ መንግሥት ነው ያለን፡፡ በበኩሌ የወያኔው መንግሥት በመጪዎቹ የሀገራችን ቀጣይ ታሪኮች «ዋ! የወያኔ ዓይነት ጭራቅ መንግሥት እንዳይመጣባችሁ!» እየተባለ አመጸኛ የኅበረተሰብ ክፍልን ለማስፈራሪያነት የሚያገለግል ይመስለኛል - ሕጻናትን ለማስፈራራት « ጭራቅ ይሰለቅጥሃል! አያ ጅቦ ይቦተርፍሃል!» እያልን እንደምናስፈራራው ማለት ነው፡፡ ስለዳግማይ ወያኔ የመንግሥትነት ሥልጣን ዘርዝሮ መጨረስ የሚቻል አይደለም፡፡ «ሰማይ ብራና ውቅያኖስ ቀለም» ቢሆኑም ተጽፎ አይዘለቅም፡፡

ይህ መንግሥት ነው እንግዲህ አሁን በዚህ ሰሞን የከተማችን ወሬ የሆነውንና በዓይነቱ በዓለማችን ልዩ የሆነ «ቅን አሳቢነት» የተገለጠበትን የወሬ ማነፍነፊያ ቅድመ ዐዋጅ (Opinion Survey) ነጠላ ዜማ የለቀቀውና ቀላል ቁጥር የሌለውን የኅብረተሰብ ክፍል እያመሰ የሚገኘው፡፡ ይህ ገና ያልታወጀ ግን ብዙ ወገኖችን ከአሁኑ እያስለቀሰና የዐዋጁን አደገኛነት በመፍራትም ከሥራ ገበታቸው በገዛ ፈቃዳቸው እንዲሰናበቱ እያደረገ የሚገኘው አሳሳቢ ጉዳይ፣ መንግሥት የግልና የመያድ (NGO) ሠራተኞችን የጡረታ ዋስትና ክፍያ (Provident Fund) ከየመሥሪያ ቤቶቹ በዐዋጅ ለቃቅሞ ወስዶ ለቅዝቁ «ማስፈጸሚያ» ሊያውለው ነው የሚባለው ነው፡፡ የዚህን መሠሪ ዐዋጅ ውስጠ ነገር የሚያውቁ ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ ይህ ዐዋጅ ከታወጀ በሁዋላ ማንም የግል ሠራተኛ ከሥራ ቢወጣ እንደበፊቱ እሱና መ/ቤቱ ያጠራቀሙትን የጡረታ ገንዘብ አይወስድም፤የጡረታ ዕድሜው ከደረሰ ከመንግሥት የጡረታ ኮሚሽን መ/ቤት በየወሩ እንደማንኛ ውም የመንግሥት ተጡዋሪ (አሥር ብርም ደረሰው ሃያ ብር) በሚዘጋጅለት የጡረታ ደብተር ይከፈለዋል፤ የጡረታ ጊዜው ገና ከሆነም አሥርም ይሁን ሃያ ዓመት ይጠብቃል - «እህል የሚደርስ በፍልሰታ እኔ እምሞት ዛሬ ማታ»፡፡ ለምን? ገንዘቡ ተወስዶ ለትራንስፎርማሽን «ማስፈጸሚያ» ውሎኣልና፡፡ ሠራተኛው ለአጣዳፊ ጉዳይ የራሱ የሆነውን ገንዘብ ቢፈልገው ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ እሱም ጧ ፍጥርቅ ይላታል እንጂ አያገኛትም፡፡ አዛኝ ቅቤ አንጓቹ የማፊያው መንግሥታችን ሀገርን በብልህነትና በአስተዋይነት የመምራት ጥበቡን ለዓለም እያስመሠከረ ያለው በዚህ መልክ ነው - ወገኖቼ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የኔ ነው የምትለው ነገር የለህም፤ የገዢው ወገን አባልና አደግዳጊ ከሆንክ ምድር ለምርጥ ልጆቹዋ የምታፈራው ነገር ሁሉ አለህ፤ አለበለዚያ ሰማይና ምድር ይመሣጠሩብህና ምድር ትከዳሃለች፤ ሰማዩ በላይህ ላይ ይደፋብሃል፡፡ ከዚያ በሁላ አንተም ያንተዎችም የለህም፤ የላችሁም፡፡ አይፍረድ ነው ግን ቀን ጎደለብንና ተፈረደብን፤ ፍርዱም አመክሮ የሌለው ሆነና ጤናማ አስተሳሰባቸውን የተነጠቁ ወያኔ ወንድምና እህቶቻችን የማይነጋ መስሎኣቸው - እሰከ ዓለም ፍጻሜም እንደፈነጠዙ የሚኖሩ መስሎኣቸው ይሄውና ካለ እማኝ ካለ ዋቢ የቁም ስቅላችንን ያሳዩናል፡፡

በዚያን ሰሞን ደመቀ የሚሉት የወያኔ ኮንዶም(ይህ ቃል አንባቢን ያስከፋብኝ ይሆን? ወድጄ አይደለም ይቅርታ) የግል የትምህርት ተቋማት ተጠሪዎች፤« በግል የትምህርት ተቋማት ላይ የተጣለው ገደብ የብዙ ሽዎች ሠራተኞችንና በሥራቸው የሚተዳደሩ ቤተሰቦቻቸውን ሕይወት አደጋ ላይ ስለሚጥል ይህም ችግር ቢታሰብበት» ተብሎ ቢጠየቅ ይህ በመለስ ሳምባ የሚተነፍስ በእናቱ ማሕጸን ቢጨነግፍ የሚሻለው በቀቀን ዜጋ፤«ኢሕአዴግ ስላላችሁዋቸው ሰዎች አይጨነቅም::» የሚል አሳፋሪ መልስ ነበር የሰጠው:: የወያኔው ኮንዶማዊ አፈ ቀላጤ ይህን በተናገረ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ የማፊያው መንግሥት ለዜጎች ተቆርቁሮ ገንዘባቸውን በዐዋጅ ሊወርስ ነው መባሉን ስንሰማ የወያኔን ጠባይ የማናውቅ ተገረምን፤ ተደመምን፤ደክፉኛ ደነገጥንም:: መሠሪ ባሕርይውን የምናውቅ ደግሞ « ምን አዬሽና? ገና እያንዳንድሽ በሚስትህና በባልሽ ግብርና ቀረጥ ትከፍያለሽ! በማን ግዛት ውስጥ በነጻ ትዋሰቢያለሽ? ለምትተነፍሽው አየርም ከሽቀጦች ዋጋና ከአገልግሎት ክፍያዎች ጋር እየተደረበ ትከፍያታለሽ! የሲዖል ትል - የገሃነም እሳት መሆናችንን ታውቂ ዘንድ የተልዕኳችን ዐቢይ ገጽታ ነውና ገና ታሪያለሽ፤ ትደብኛ ለሽ! ምናባሽስ ታመጫለሽ?» እያልን ቀለድን፤ «ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ»ንም ጨመርንባት:: «ጊዜ እስኪያልፍ ያባትህ ባሪያ ይግዛህ» ብለንም የሃበሻኛይቱን የሽንፈት ማለባበሻ ተረት አከልንባት - ለጊዜው ሁሉም ነገር ተወነባብዶብን በጨለማ ውስጥ እዬዳከርን መኖራችንን እያወቅነው:: ሌላ ምን ምርጫ አለን? ለአሁኑ ምንም!

እዚህ ላይ በተለይ ለዲያስፖራው ላስተላልፈው የምፈልገው አጭር መልዕክት አለኝ:: እናንተ ባትኖሩ ኖሮ እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን ስንትና ስንት የኑሮ ፈተና ይገጥማቸው እንደነበር መረዳት አስቸጋሪ አይደለም:: ከአራቱም የሀገራችን ክፍሎች በጨካኙ የደርግና በአረመኔው የማፊያ ቡድን መሪር አገዛዞች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግሮች ምክንያት ከሀገር የተሰደዱ ወገኖቻችን ከሚያገኙዋት እያጋሩ ቤተ ዘመዶቻቸውንና ወዳጆቻቸውን ባይደጉሙ ኖሮ ብዙው ሕዝብ ምን ዓይነት የመከራ ኑሮ ሊገፋ እንደሚችል መገመት አይከብድም:: በዚያም ላይ ቀረጥ እንዳይጥል የወያኔን ጆሮ ይድፈንልን:: እንዴ? ዋና የሀገር ማስተዳደር ሥራቸው እኮ ገንዘብ ያለችበትን ሁሉ እያሻተቱ በዚያች መከረኛ የዐዋጅ ልምጫቸው ማታ ልክ እንደደርግ ቲሪሪም ቲሪሪም አድርገው ገቢ አድርጉ ነው የሚሉ:: የጣለብን ወሬዛ እኮ የዋዛ አይደለም - መገላገያውን በቶሎ ይስጠን እንጂ:: ዲያስፖራው የግል ቤተሰቦቹን በተቻለው እንደሚደግፍ ሁሉ ምንም መከታና ደጋፊ ለሌለው ለእንደኔ ዓይነቱ የወያኔ ተጠቂም ማሰብ ይጠበቅበታል፤ ወገናዊ የሞራል ግዴታም አለበት:: ስለዚህ እናንተ በውጭ ሀገር የምትኖሩ በተለይ በደህና የኑሮ ደረጃ ላይ የምትገኙ ወገኖቻችን በኅጥና በሃይማኖት ያልተከፋፈለ እውነተኛ የትግል ግንባር በማቋቋም ወይም ከቋቋሙት ውስጥ የተሻለ ነው የሚባለውን በማጠናከር ጠቅላላውን ሳንጠፋ በነፍስ ድረሱልን:: የናንተ በጎራና በሚና ተቧድኖ በነገር ወንጭፍና በድረ ገጽ እንካስላንትያ መናቸፍ ጣራችንን ያራዝም እንደሆነ እንጂ በጭራሽ መፍትሔ አላመጣም - አያመጣምም፤ ለብዙ ዓመታት ታይቶ የተረጋገጠውም ይሄው ነው:: ሕዝቡ አያውቅም አይባልም - ሁሉን አብጠርጥሮ ያውቃል:: ማን አጭበርባሪ፤ ማን አፈኛና መሠሪ፤ ማን የሥቃዩ ዋና መንስኤና ለመከራ ኑሮው ተራዝሞ መቀጠል ምክንያት እንደሆነ በሚገባ ያውቃል:: የሚጠብቀው ታሪክ የማይቀር ፍርዱን እስኪሰጥ ብቻ ነው:: እንክርዳዱ ከፍሬው ፤ ምርቱ ከግርዱ የሚለይበት የቁርጥ ቀን ሲመጣና «እዩኝ እዩኝ» የተባለውን ያህል «ደብቁኝ ደብቁኝ» ማለት ግድ ሲሆን ያኔ ታሪክና ሕዝብ በ«ለለአሃዱ በበምግባሩ» ነባር የፍትሕ ሥርዓት ሁሉም የየመክሊቱን ማግኘቱ የማይቀር ነው:: ያኔ ዕውቀት አይጠቅምም፤ ያኔ የሀሰትና የፈጠራ ድርሰት ማነብነብ ምንም አይፈይድም:: ያኔ በመጽሐፉ «ጌታ ሆይ በስምህ ለተራቡ አብልተናል፤ ለታረዙ አልብሰናል. . .» ብለው ክርስቶስን ቢጠይቁት « የምትሉት ሁሉ ሀሰት ነው፤ ይልቁናስ ወደተዘጋጀላችሁ የዘላለም እሳት ሂዱ(ለራሴ እንደሚመች ያቀናበርኩት)» ብሎ እንደገለጸላቸው የኛዋ ኢትዮጵያም « እማ ኢትየጵያየ - ስንትና ስንት ገንዘብ ለዚህና ለዚያኛው ተቃዋሚ ሰጥጫለሁ፤ ስንት ጽሑፎችን ተደብቄ ከድረ ገጽ አንብቤያለሁ . . .» ብሎ ሊያምታታት የሚሞክርን ብኩን ዜጋ፤ « አንት የተረገምክ ልጄ ከፊቴ ዘወር በል:: ለጡት ነካሽ አራጆቼና አካሌን በላቾችም ስታዋጣ ነበር - ለምቾትህ አድልተህ:: ስንቶች ላንተው ነጻነት ሳይቀር ሞትን በጠራራ ፀሐይ ሲጋፈጡ፣ ካለ አበሳቸው እሥር ቤት ሲታጎሩና ለስደት ሲዳረጉ አንተ ትሳለቅባቸውና ከገዳዮቼም ጋር ትሽራሞጥ ከርስህንም ወደህ በውስኪና በጮማ

አብረህ ጮቤ ትረግጥ ነበር፡፡ አንተ ለኔ የዘመኑ ይሁዳ ባንዳ ነህ፡፡ . . .» የሚል መልስ በማግኘት ውርደትን መከናነብ እንደሚኖር ቅንጣት የሚጠራጠር ዜጋ እንዳይኖር፡፡ «ሁሉም ለበጎ መሆኑ » እንዳለ ሆኖ የተንሸዋረረ አካሄድን ብዙ ሳይመሽ ማስተካከል ከአስተዋይ ሰው የሚጠበቅ ነው፡፡ አንድ ሰው ትናንት አጥፊ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ከሌሎች እንስሳት በተለዬ ፈጣሪ የሰጠውን አንጎል ተጠቅሞ ራሱን በመፈተሽ አስተሳሰቡንና አቋሙን ቢያርቅ (ር'ን ጫን ማድረግ) ያምርበታል እንጂ አያስጠላበትም፡፡ ዕድሜ ልክ ግትር ሆኖ መዝለቅ የሰው ልጅ ባሕርይ መገለጫ አይደለም፡፡ «አንገት የተፈጠረው ዞሮ ለማየት ነው» ይባልስ የለም? እዚህ ላይ ሲፈጥረው ድፍን ቅል ራስ ወይም ባልጩት ጭንቅላት ለሆነ ከማይጠቅም ግዑዝ ነገር የማይለይ ዜጋ ግን አንዴውኑ ተፈጥሮ ተጫውታበት ተበለሻሽቶኣልና እሱን ለመምከር መሞከር ድንጋይ ላይ ውሃ እንደማፍሰስ ነው - ምክሩንም ከስድብ ነው የሚቆጥረው፤ ሆዱ ነዋ አሳዳሪ ጌታው- ሆዱን የሚወድ ደግሞ ሀገርን ቀርቶ ፍቅርን አያውቅም፤ ፈጣሪንም እንዲያውቅ አይጠበቅበትም ፤ ፈጣሪም ፍቅር ነውና፡፡ ልብ ያለው ልብ ይበል፡፡ የክህደት ዘመን መቋጫው ተቃርቧል፡፡ «ጨለማው ሲበረታ ንጋት መቃረቡን ትረዳላችሁ» ተብሎ የተጻፈው በየትኛው መጽሐፍ ነበር? ዘነጋሁት፡፡

እዚህ ድረስ ወርደው የብሶት ደብዳቤየን አንብበውልኝ ከሆነ ምሥጋናዬ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ፈቃደኛ ሆነውልኝ ከዚህ በታች በተቀመጠው አድራሻ ማንበብዎን ጠቅሰው - አስተያየት ካለዎትም ጨምረው - ቢመይሉልኝ ከልቤ እወድዎታለሁ፤ ለነገሩ ባይልኩልኝም ለርስዎ ያለኝን ውዴታ የሚለውጠው የለም - ምክንያቱም ከፍቅርና ከመዋደድ በስተቀር የሰው ልጆችን እግር ከወርች ቀፍድደው ያሠሩዋቸውን ሁለንተናዊ ችግሮች ለማስወገድ አሁን ባለው ነባራዊ የዓለም ሁኔታ ሌላ ተጨባጭ መፍትሔ የለም ብዬ አምናለሁና፡፡

**yiheyisaemro@gmail.com**